ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ
Coalition for Unity and Democracy Party (Kinijit)
www.KINIJIT.org

# ‹‹ለሕዝብ ስሜት ግድ የሌላቸው ፖለቲከኞች ሩቅ አይጓዙም››

## ከቅንጅት የፓርላማ አባላት የተሰጠ መግለጫ

በቅንጅት ከፍተኛ አመራሮች መካከል የተፈጠረው የአቋም ልዩነት የፓርቲውን አባላትና ደጋፊ በእጅጉ ያሳዘነ ክስተት ሆኖ ቆይቷል፡፡ የተፈጠረው የአመራሮቹ የአቋም ልዩነት በሰከነ መንፈስ በጠረጴዛ ዙሪያ ተፈቶ አንድና የተጠናከረ ቅንጅት ሆኖ እንዲቀጥል የመላ አባላቱና የፓርቲው ደጋፊዎች ፍላጐት መሆኑን ተረድተናል፡፡ አስታራቂ ሽማግሌዎቹም ይህን የአንድነትና የእርቅ ተግባር ለማጠናከር እየሰሩ ባሉበት ሰዓት እርቁን እንፈልገዋለን በሚል አስመሳይ አነጋገር ለልዩነቱ መባባስና ‹‹ቅንጅት በየፊናው ይሂድ›› የሚለውን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ የሚንቀሳቀሱ የቅንጅት አመራሮችና የፓርላማ አባላት ቡድን መኖራቸውን ለማወቅ ችለናል፡፡ በተለይ የፓርላማ ተመራጭ የሆንን የቅንጅት አባላት እንደ ሕዝብ ተመራጭነታችን ልናፀባርቅ የሚገባን የመረጠንን ሕዝብ ፍላጐትና ስሜት ሊሆን እንደሚገባ እናምናለን፡፡ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ እንዲኖር የዘወትር ምኞቱን ለማሳካት ቅንጅት ሳይከፋፈል አንድ ሆኖ እንዲቀጥል የማድረግ ትልቅ ኃላፊነት እንዳለብን እናውቃለን፡፡ ይሁን እንጂ የአመራሩ መከፋፈል ሠርግና ምላሽ የሆነላቸው የፓርላማ ተመራጮች ከዚህ በተቃራኒ በሆነ መልኩ ሲንቀሳቀሱ ይስተዋላሉ ይሄውም፡፡

1. በአቶ ተመስገን ዘውዴ የሚመራው የፓርላማ ቡድን ከመረጣቸው ሕዝብ ፍላጐትና ስሜት ውጭ ለራሳቸው ሥልጣን ለማግኘት በማሰብ ከእነ ወ/ሪት ብርቱካን ቡድን ጋር ተዋህደናል ከማለት አልፈው የተጓደሉ የላዕላይ ምክር ቤት አባላትን ለማሟላት ሌላውን የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት በማግለል የላዕላይ ምክር ቤት አባላትን አሟላን ማለታቸው ከፓርቲው ሕግና ደንብ ውጭ ሆኖ ለተደበቀ የሥልጣን ፍላጎታቸው መንቀሳቀሳቸውን ለመረዳት ችለናል፡፡

2. የእነ አቶ ተመስገን ዘውዴ ቡድን በፓርላማ ውስጥ ይዞት የነበረው ሥልጣን በአቶ አየለ ጫሚሶ በመነጠቁና በቅንጅት አመራር መካከል የተፈጠረውን ልዩነት መጠቀሚያ በማድረግ ከጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ውጭ አዲስ ፓርቲ ለመመስረት መወሰኑና በዚያም ውስጥ ወ/ሪት ብርቱካንን ሊቀመንበር አቶ ተመስገን ዘውዴን ም/ሊቀመንበር በማድረግ የሥልጣን ክፍፍል ማድረጉ ለሕዝብ ስሜት ግድ የሌላቸውና ቅንጅትን ለማፍረስ ፍላጎታቸውን ያሳዩበት አጋጣሚ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. ይሄው የአቶ ተመስገን ዘውዴ ቡድን የእነ ወ/ሪት ብርቱካንን ቡድን ደግፎ የተፈጠረው የቅንጅት አመራሮች ልዩነት እንዳይፈታና ቅንጅት ተከፋፍሎ እንዲሄድና ስሙንም እንዲያጣ አስተዋጽኦ ከማድረግ በተጨማሪ ሌላ ፓርቲ ማቋቋሙ በአስታራቂ ሽማግሌዎቹም ላይ ትልቅ እንቅፋት እየሆነ መጥቷል፡፡ ይህንንም የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያውቀውና አብረዋቸው የተሰለፉ የፓርላማ አባላትም ከዚህ አፍራሽ ድርጊት ራሳቸውን እንዲያገሉ በመረጣቸው ሕዝብ ስም ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡

4. የእነ አቶ ተመስገን ዘውዴ ቡድን ትላንት መሪዎቻችን በቃሊቲ እስር ቤት በነበሩበት ሰዓት አመራሩን ክዶ የቅንጅትን ሥልጣን በአቋራጭ በእጁ ለማስገባት አዲስ ቅንጅት ለመፍጠር ወደኋላ ያላለ እና ፓርላማ ያልገቡ የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎችን ያወገዘ ሲሆን ዛሬ ደግሞ የቅንጅትን አመራር ልዩነት በማስፋትና በማራገብ ቅንጅት ለሁለት እንዲከፈል በሰፊው እየተንቀሳቀሰ ያለ ቡድን ሆኗል፡፡ እኛም የቅንጅት የፓርላማ አባላት የእነ አቶ ተመስገን ዘውዴን እንቅስቃሴ በእጅጉ እያወገዝን የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎቹ ይህን አፍራሽ ሂደት እንዳይከተሉት በቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ስም ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡

ቅንጅት አንድ ነው

ጥር 26 2000 ዓ.ም

አዲስ አበባ